# ብሔር አልባ እስረኞች

ቴዎድሮስ ነጋሽ (ማኅደረ)



ዛሬ ጽሑፌን የምጀምረው በምወደውና በማከብረው በዘመናችን ትልቅ ሰው በኔልሰን ማንዴላ ታዋቂ ጥቅስ ነው፡፡ "The greatest glory in living lies not in never falling, but in rising every time we fall." -Nelson Mandela የሕይወት ትልቅነትና ውዳሴ ጸንቶ የሚቆመው ባለመውደቅ ላይ ሳይሆን በወደቁ ቁጥር ፈጥኖ በመነሳት ላይ ነው፡፡ ስንወድቅ የሚሰድበን ስንነሳ የሚያወድሰን ብዙ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተደጋገመ ክስተት በመሆኑ ሳናፍርበት የምንተገብረው ድርጊት ነው፡፡ በሃገራችን ያለው የለውጥ መንፈስ ሲያስደስተን ቆይቶ እሚያሰጋን ደረጃ ላይ ሲመጣ “ወዴት እየሄድን ነው?” ብለን እራሳችንን እንጠይቃለን፡፡ መልስ የሚሰጠን ፈልገን ሳይሆን መጠየቁ ሌላውን እሚያነቃው እየመሰለን ነው፡፡ እወድሻለሁ ያለ ሁሉ በፍቅር የተቃጠለ አይደለም እንዲሉ ማለት ነው፡፡

የቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት ከሥልጣን ሲወርድ፣ ሁሉንም በቢሮክራሲው ውስጥ የነበረውን ሁሉ አድሃሪ ነው ብለን ኮነንን፡፡ ባለስልጣን ማለት ደግሞ ቃሉ እራሱ የተጠላ ሆነ፡፡ ዛሬ በወቅቱ የነበሩትን ባለሥልጣናት የእውቀትና የሥራ ብቃት የዲፕሎማሲ ብስለት ስናገናዝብ ያልበሰለ አመለካከት ይዘን እንደ ጋለብን ብዙ የሚያጨቃጭቅ አይሆንም፡፡ የፊውዳሉ መንግሥት መውረድ እንደነበረበት ስንስማማ፣ በውስጡ የተሰለፉትን የሃገሩን ምሑሮች ያለፍርድ መግደል ግን ከወንጀልም ወንጀል ነበር፡፡ ሚኒስትሮችን በመግደል የጀመረው የለውጥ ማአበል የወጣቶችን ደም እንደካምቦዲይው የካሜሩጅ የግፍ ጭፍጨፋ ደም ለማፍሰስ ግዜ አልወሰደበትም፡፡ ያ የደም ስካር ተራማጅ ናቸው የምንለውን ሁሉ አረደ፡፡ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን አጠፋለሁ ብሎ ተነሳ፡፡ ስልጣን ሱስ መሆን ሲጀምር አብሮ የተሰለፈውንም ጭምር በገመድ እያነቀ በጥይት እየቆላ ማጥፋቱን ቀጠለ፡፡ የግለሰብ ተክለ ሰውነት ተጠናክሮ ሻለቃው ኢኮኖሚስት፣ ፖለቲከኛ፣ መሃንዲስ፣ የግብርና ጠበብት፣ ዲፕሎማት ናቸው ተባለ፡፡ በክፉ ያነሳቸው ሳይሆን ሊያነሳ ያሰበ ተረሸነ፡፡ በፓርቲ ምስረታ ላይ ሻለቃው የሲቪል ካባቸውን ሲለብሱ **“የሳቸው መወለድ ለኛ ተስፋ ነው”** ብለው ምሁር ነን ባዩ ተናገሩ፡፡ **“ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም”** የሚለው መፈክር **“የአንድ ጓድ ደም በሺ የአድሃሪ ደም ይመለሳል”** ተባለና ቀይ ሽብር ተጀመረ፡፡ ሽብር የሚለውን ከሣቴ ብርሃን የአማርኛ መዝገበ ቃላት **“ድንገተኛ አደጋ፣ ወራሪ፣ መጥቶ አገር ከተማ መሸበር፤ መተራመስ፤ በድንጋጤ ወድቆ መርበትበት፡፤”** በማለት ይገልጹታል፡፡የተቃዋሚ ወገን ደግሞ “**ባንዳ**” የሚለውን ከወራሪ ጠላት ጋር የወገነ የሚለውን በመቀየር ከኔ ጋር ያልቆመ ሁሉ የተፈርጀ ነው ብሎ ቃሉን ሲጠቀምበት ቆየ። ጎራ ለይተን ተጨራረስን ፊዳሉን መንግሥት አወረድሁ ያለው የገዳይ ስብስብ በሕዝብ ትግል ተንኮታኮተ።




ዛሬ አለንበት ለመድረስ የብዙዎች መሰዋእትነት ተከፈለ። ያንን መስዋእትነት የከፈሉት ሳይመሰገኑ **“የስልሳዎቹ ያመጡብን ጦስ”** ሁሉ ተባለ።

ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ እንቁላል ነበር ይህን ጊዜ አበሻ።

ጭንቅ ያለው፣ “ለእኔ እናት ምን እረባት አንዱም ድንጋይ አንዱም አፈር ጫነባት” ሲል ይሰማል።
ለተስፋችን ድጋፍ ከሚሆን ቃል ይልቅ ለእርግማናችን የሚሆን ቃላት በመምርጥ እንካናለን፡፡



ታዲያ ዛሬ ለሕዝብ መብት እታገላለሁ ብሎ ወጣትነቱን በትግል ገድሎ የኖረውን ማንም ሊከፍለው ከሚችለው በላይ መከራን ተቀጣጥሮ የጥይት ባሩድ አሽቶ ወንድም ዘመዱን፣ ጓደኛ፣ ጓዶቹን ገብሮ፣ በአሽናፊነት የገባውን፣ በትግል መሃል አድጎ በትግል መሃል የተማረውን፣ ተመክሮና አመለካከቱን በመጻፍ ለሕዝብ ያበረከተውን በርከት ስመኦንን በእስር ካላስገባነው ችግር ይፈጥራል በሚል ከጓደኛው ጋር ከታሰረ እነሆኘ ዓመት ሞላ፡፡ በዓመት መፍረድ ያልተቻለበት ወንጀል ደግሞ ወንጀል አይሆንም፡፡ ሙስናን በመዋጋቱ የሚደነቀው በረከት በሙስና ተወነጀለ፡፡ የተጻፉት መጽሕፍት ግን የሱን በሙስና አለመጠርጠር ይመሰክራሉ፡፡ በስብሰባ ላይ የተናገራቸውን በጽናት የቆመባቸውን አቋሞች ስናነብ ደግሞ የታሰረው በሙስና ሳይሆን ብዙ በማወቁ ነው ብለን ደመደምን፡፡ በረከት ምንም ጥፋት አልሰራም የሚል ያለ እስካሁን አላጋጠመንም። የሰራውን ግን የሰሩት በጅምላ እንጂ በተናጠል አልነበረምና ሌሎች በብሔር ሲሸፈኑ በረከት ብሔር አልባ ሆነ፡፡ የተወለደበት የታገለለት ሳይሆን DNA ው ተፈትሾ የውጭ አገር ዜጋ ነው ተባለ፡፡ የተወነጀለበት አገር መሪ ደግሞ **“ከሱ የከፉ ጠላት የለንም”** ሲሉ ተደመጡ፡፡ ለሃገር የዲሞክራሲ መብት ለብሔር አንድነት የታገለው በረከት ከጓደኛው ጋር ሆኖ ብሔር አልባ በመሆኑ እስርቤት ተወረወረ፡፡ የመለመሏቸው ታጋዬች ያሰለጠኗቸው ጓዶች አሳሪ ሆኑ ጠባቂ ሆነው ተመደቡ፣ ዳኛ ሆነው ተሰየሙ። በቆየ አባባል አብዬት ልጆቿን በላች፡፡

በረከትም ሆነ ታደሰ አማራ ለመሆን የአማራ ደም እንደሚያስፈልግ እንዲገባቸው እየተደረገ እንደሆነ አሁን የሚረዱት ይመስላል፡፡ እንደነሱ ሥልጣን ላይ የነበሩት ጓዶቿቸው ኦሮሞ የሆኑት በክልላቸው ትግራይ የሆኑት በክልላቸው ሲዳማ የሆኑት በክልላቸው ሲጠለሉ እነሱ መጠለያ አጥተው በዝናብ ይደበደቡ ጀመር። ዓመት ሙሉ መረጃ ማቅረብ ያልቻለ መንግሥት ካሁን በኋላ የሚያቀርበው ምንም ነገር ውሃ የሚቋጥር አይሆንም፡፡ ምርጫው እስኪደረግ በማረፊያ ቤት ይቆዩ ማለት ከሆነ ደግሞ የሚናገሩት የሚያሳምን ነገር ይዘዋል ማለት ያስመስላል፡፡ ከሆነ ይህ ደግሞ እስራቱ የፖለቲካ እንጂ የሙስና አይደለም ማለት ነው፡፡ ለምን ዝም አትልም ብሎ ማሰርና ዝም ካላልክ ነገር ፈልጌ አስገባሃለሁ ማለት ሁለቱም አንድ ናቸው፡፡



በኦሮሚያ ያሉ አማሮች መብት መከበር አለበት የሚል ቡድን፣ ግለሰብ፣ ፓርቲ በአማራ ክልል ያሉ ዘራቸው አማራ ያልሆኑትን እናስራለን ካለ ትልቅ የማይወጣው መቀመቅ ውስጥ እየገባን መሆኑን ይጠቁማል፡፡ የማይገባኝ ነገር በረከት ለኤርትራ የቆመ ነው ከተባለ እንዴት የኤርትራ መንግሥት በጠላትነት ሲፈርጀው እናስተውላለን፡፡ የለም ለኤርትራ ሳይሆን ለትግራይ ሕዝብና ፓርቲ ያደሉ ነበር ከተባለ ለዛ ያላደላ ማ ነበር? የሚናገሩትን ማቆም አልተቻለም ከሆነ ክሱ ይህ ፖለቲካዊና ኢ ዲሞክራሲያዊ አይደለምን? የደርግ ባለስልጣናት ይለቀቁ ብሎ ምሕረትን መቀበል አለብን ያለው በረከት ቢያጠፉ  እንኳን ለምሕረት እንዴት አልበቃም፡፡ ዛሬ የፈረጁበት ፈራጆች ነገ የነሱም እድል ሲመጣ ምን ይሉ ይሆን?

ሲታገል የኖረው ጎንደሬው ከሰረ፣
ብሔር አልባ ሆኖ በረከ ታሰረ፡፡
ምስጋና ክብር ይሁን አንተ እንደታገትከኝ፣
መሸሸጊያ ብሔር እንኳን አልነሳኸኝ፡፡
ለዲሞክራሲ መብት ብረት ያነሳችሁ፣
አበስኩ ገበርኩ በሉ ንስሐ ገብታችሁ፣
መታሰር አይቀርም ብሔር ከሌላችሁ፣
በረከትን እዩ ትምህርት ይሁናችሁ፣
ታደሰን አስተውሉ ጠፍቷል ከጎናችሁ፡፡




በጣም የምፈራው ደግሞ በህመም ላይ ናቸው የተባሉት እነዚህ የፖለቲካ እስረኞች በእስራት ላይ እያሉ በእስር ላይ ከሞቱ ነው፡፡ ያ ለዓመታት የሚያነጋግር ነገር ይሆናል ብዬ እፈራለሁ፡፡ በኢትዮጵያዊነት እንጂ በዘር አላምንም የሚል ደግሞ ለእሱ ሲያመቸው በብሔር ሰውን መፈረጅ ትክክል ነው ብሎ እንዴት ሌላውን ሊያሳምን ይችላል? ከበረከትም ሆነ ከታደሰ ጋር ብረት አንግቤ አብሬ በትግል ተሰልፌ ታግያለሁ፤ በተለያዩ ወቅቶችና አጋጣሚዎች በስምምነት በልዩነት ተወያይቻለሁ፤ አንድ የማወቀው ነገር ቢኖር በረከት የሃሳብ ባለጸጋ መሆኑን እንጂ የገንዘብ ባለጸጋ አለመሆኑን ነው፡፡ በህይወት ዘመኑ ሰቀላ ቤት እንኳን ያልሠራን ግለሰብ ቤት ከሌለህ እስር ቤት እንከትሃለን ማለት ሕግ ካለ ወንጀል መሆን ነበረበት፡፡ በረከትንም ሆነ ታደሰን በጽናትና በብርታታቸው እንጂ በድክመታቸው አላውቃቸውም፡፡ እስከዛሬ መጻፍ አልሞከርኩም ነበር አንሁን ግን ዝም ማለት መሸነፍ ነው አልኩ፡፡ ብአዴን ሲቋቋም የጥንስሱ አባል በመሆኔ የምኮራ ሰው ነኝ፡፡ በረከትንም ሆነ ታደሰን ኢሕአፓም ሆነው ብአዴን ሆነውም አውቃቸዋለሁ፡፡ የሚሰማቸውን በመናገር የማይግባቡበትን በመወያየት ጽናታቸው ይማከብራቸው ናቸው፡፡ እንደነሱ በትግሉ መሃል ቆይቼ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ባልገባም ለማሸነፋቸው የእኛም ሆነ በገጠርና በከተማ የተሰውት ጓዶቻችን እጅ እንዳለበት ግን ለሰኮንድ አልጠራጠርም፡፡

አንዳንዶች እሱም በዘመነ ሥልጣኑ ሲያስር ነበርና መታሰር አለበት የሚሉ አጋጥመውኛል፡፡ ከሆነ የእሱ ስህተት ለሌላው ስህተት ድልዳል መሆን አይችልም፡፡ መታገል ያለብን ለእውነትና ለፍትህ ነውና፡፡ ያሰሩ ይታሰሩ ከተባለ ደግሞ አሳሪዎችንም ማሰር ሊመጣ ነው፡፡ ጎንደር ተወልዶ ያደገውን ጎንደሬ አይደለህም ካልን አርሲ ተወልዶ ያደገውን አርሲ አይደለህም ማለት ቢመጣ እንዴት እንከላከላለን፡፡ የእኔም የአራት ኪሎ እድገቴ አፈር ሊበላ ነው፡፡ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ነች እያልን አንድነታችን ይጠቅማል ብለን እየተናገርን በረከት ኤርትራዊ ነውና ስለአማራው መብት መናገር አይችልም ማለት አይጣረስም? ለምን በብሔር ሳይሆን በአገር በኢትዮጵያዊነት እንሰባሰብ ሲባል ሁላችንም ስለምንሰማ ማለቴ ነው፡፡

የልዩነት ሃሳብ ለእድገት መሰረት መሆኑ እውነት ነው
የኢትዮጵያም ዘላለማዊነት የማይሸረሸር አለት ነው፡፡